

# ❧ 8 ☙

# ተቀናቃኝ (ዜለት)

## 8-1

ባለፈው ቁጥር 7 ትምህርታችን ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን በአይሁድ መካከል በጣም ጎልተው የሚታዩ ስድስት ዓይነት እንቅስቃሴዎች (ፓርቲዎች) እንደነበሩ መግለጻችን ይታወሳል። በዛሬው ትምህርታችን ከእንቅስቃሴዎች መካከል አይሎ ይታይ የነበረውን የተቀናቃኝ (ዜለት) ክፍል እምነትና ተግባር እናያለን። ተቀናቃኝ (ዜለት) የተባለው ስም የተሰጣቸው በአንደኛው ዓመተ ምህርት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ለአይሁድ ሕዝብና ለአገራቸው ጥብቅ የሆነ ፍቅር ለነበራቸው ለአገር ወዳድ አይሁዶች ነበር። የአይሁድን ሕዝብ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ሕይወታቸውን እስከ ማጣት ደረጃ ቢያደርሳቸውም በጥብቅ ሳይታገሉ የሚያልፉ ክፍሎች አልነበሩም። እነዚህ የአይሁድ ክፍሎች የመ ጨረሻው ውጤት ጥሩ እስካልሆነ ድረስ መግደል፣ ማጥፋት፣ ማቃጠል ልክ ነው ብለው የሚያምኑ ናቸው። እነዚህ ተቀናቃኝ የተባሉት ክፍሎች አርአያ አድርገው ይመለከቱት የነበረው የአልአዛርን ልጅ ፊንሀሳንን ነበር። ይህ ሰው የእግዚአብሔርን ስም ያጎድፋል ብሎ ያለውን ሰው ከድንኳኑ በመግ ባት በሰይፍ ወግቶ እንደገደለው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል (ዘሁል. 25፥7-13)። ይህ ተቀናቃኝ (ዜለት) የተባለው ፓርቲ በጣም የታወቀው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ6ኛው ዓ.ም. ነው። ይኸውም ይሁዳ የሮም የቀኝ አገዛዝ ሥር በነበረችበት ጊዜ፥ ሮም የአይሁድ ሕዝብ ቁጥር ይታወቅ ብሎ ትዕዛዝ በሰጠበት ጊዜ ገሊላዊው ይሁዳ የሮምን ትዕዛዝ ተቃወመ። ይህም በሁለቱም ወገን ሰይፍ እንዲማዘዝ አደረገ። የተቀናቃኝ ፓርቲ ጦር መምዘዝ ትክክል ነው በማለት ምክንያታቸውን በመግለጽ ለማስረዳት ይሞክሩ ነበር። አይሁዳውያን ለሮም ቀርጥ አንከፍልም ንጉሥም ደግሞ እንደማንኛውም ሰው እንጂ አምላክ ስላልሆነ ለንጉሥ አንሰግድም” ይሉ ነበር። የእሥራኤል ሕዝብና ምድራቱም የተቀደሱ በመሆናቸው አገራቸውን ለቀው እንደማይወጡና በሌላ እጅ እንዳማይገዙ ወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ጠላቶቻቸውም እንዲያውቁላቸው ያደርጉ ነበር።

እሥራኤልን የሚገዛ እግዚአብሔር እንደሆነና ከዚህ አገዛዝ ሥርዓት ውጪ መሆን በዜለት እምነት እንደ ክህደት ይቆጠር ነበር። ብዙ አይሁዶች ይህንን እምነት ይደግፉ ስለነበር፥ እንቅስቃሴው በጣም አደገ። ሮም ይሁዳን በግዛታቸው ሥር በማድረግ በቀላሉ ለመግዛትና ለማስተዳደር እንዳ ይችሉ ይሄ የተቀናቃኙ ቡድን አስቸጋሪ አድርጎባቸው ነበር። ክርስቶስ በሰላም የሚያምን ቢሆንም የተቀናቃኙ ፓርቲ ወገን የሆኑትን አልተቃወመም። እንዲያውም ከመካከላቸው አንደኛውን የራሱ ደቀመዝሙር አድርጎት ነበር። ይሁን እንጂ የክርስቶስ ጠቅላላ ትምህርቱ የተመሠረተው ሰይፍ በመ ምዘዝ ላይ ሳይሆን በሰላም በመሆኑ፥ ተቀናቃኙ ስምያን ሙሉ እምነቱና ፍልስፍናው መለወጥ ነበረበት። በጥላቻና በጠብ መንፈስ የተሞላው ሕይወቱ ተለውጦ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚስፋፋበትን የሰላም ወንጌል ይሰብክ ነበር። ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን በዙሪያው ይካሄዱ የነበሩት ልዩ ልዩ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ዛሬ ዓይነታቸውና ይዘታቸው በመጠኑ መልካቸውን ይቀይሩ እንጂ የጠፉ አይደሉም። በዘመናችን ፈሪሳውያን እዳሉ ሁሉ ተቀናቃኞችም (ዜለት) አሉ። ጠቅላላ አቋማቸውና እምነታቸው የጥንቶቹን አይምሰል እንጂ የተቀራረበ መልክ አላቸው። የዘመኑ ዜለቶች (ተቀናቃኞች) ከእነርሱ እምነትና ሃሳብ ጋር የማይስማማውን ሁሉ አጥብቀው ይዋጉታል፤ ትግላቸው

የጌታን መንግሥት ለማስፋፋት ሳይሆን የራሳቸውን ተከታይ ለማብዛት ነው። በዙሪያቸው በመሰል ተቀናቃኞች መከበባቸው ብቻ ሳይሆን ሌላውን በመዋጋታቸው የታወቁ ናቸው። የዘመኑ ተቀናቃኞች መሣሪያቸው በዓይን የሚታይ ሰይፍና ጦር ሳይሆን ድብቅ መሣሪያ አላቸው። ይኸውም፥ ስለሌሎች ድካምና ውድቀት ማውራት የክርስቶስን ቁንጅና እንደሚያሳይ የተረዱት አይመስልም። ስለሆነም፥ ከምስጋናቸው ይልቅ ክሳቸው ያይላል። በዮሐንስ ራዕይ ላይ ሰይጣን "የወንድሞች ከሳሽ" የሚል ስም ተሰጥቶት እንደነበረ የተገነዘቡት አይስመስልም።

## ውጊያችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም

ውጊያችን ከሰይጣን ጋር እንጂ ከሥጋና ደም ጋር አይደለም። ማሸነፍ የምንችለውም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ በራሳችን ትግል አይደለም። ዳዊት ሊገጥመው የመጣውን ፍልስጤማዊው ጎልያድን "ይህም ጉባኤ ሁሉ እግዚአብሔር በሰይፍና በጦር የሚያድን እንዳይደለ ያውቅ ዘንድ ነው። ሰልፉ የእግዚአብሔር ነውና እናንተንም በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል" ብሎ አለው (1ኛ. ሳሙ. 17፥47)።

## ውጊያው (ሰልፉ) የእግዚአብሔር ነው

1. እውነት፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ ቅድስና፣ ትክክለኛነት ከእግዚአብሔር ስለሆኑ፥ እነርሱን ለመጠበቅ እኛ እማናደርገው ትግል ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው (መዝ. 45፥4)።
2. ቅድስና በዓለም ሲመሠረት እግዚአብሔር ራሱ ይከብራል። ያንን የሚቃወም ሁሉ እግዚአብሔርን ይቃወማል። እርሱን የሚቃወሙትንም ለመበቀል የራሱን ውጊያ ራሱ ስለሚያካሂድ፥ የእኛ ውጊያ ምንም ዓይነት ሥፍራና ኃይል አይኖረው።
3. ውጊያው የእርሱ ይሁን እንጂ እኛም ድርሻ የለንም ማለት አይደለም። በትዕዛዙ ሥር የምንውልና ስለቅድስና ሕይወት የምንዋጋ የእምነት ታጋዮች ነን (1ኛ. ጢሞ. 6፥12)። ቢሆንም ኃይላችን መንፈስ ቅዱስ ነው። ያለ እርሱ አንዳች ማድረግ አንችልም።

## ውጊያችን መንፈሳዊ ነው

1. መንፈሳዊውን ውጊያ በሥጋዊ መሣሪያ ማካሄድ አይቻልም። ጠመንጃው የክርስቶስ ጥይቱን (ቀለሁ) የሰይጣንን አድርጎ ማሸንፍ አይቻልም። የሰይጣን ጥይቶች (ቀለሆች) ጥላቻ፣ ምቀኝነት፣ አድመኛነት፣ ወዘተ ናቸው (2ኛ. ቆሮ. 10፥4)።
2. በሥጋችን እንዋጋም፣ እንታገልም አልን እንጂ ደካሞች ናቸው ብለው ሌሎች እንዲያጠቁን ወይንም እንዲጠቀሙብን አንፈቅድም።
3. ትግላችን መንፈሳዊ ስለሆነ የትግላችን ምክንያት ለራሳችን ክብር ሳይሆን ስለክርስቶስ ክብር ብቻ መሆን አለበት።
4. ውጊያችን መንፈሳዊ ስለሆነ የእምነት ትግል ነው፤ በእግዚአብሔር በመተማመን የሚገኘውን ኃይል ሌሎች ባያዩትም እኛ እናየዋለን። የክርስቲያኖችን እምነትንና መሰብሰባቸውን አጥብቆ የሚጠላና እነርሱን ለማሳደድ ቆርጦ የተነሳ አንድ ሰው ነበር። ይህም ሰው አንድ ቀን ሁለት ጣቶቹን እያንቀሳቀሰ "እነዚህን ሁለት ጣቶች ታያለህ? ታዲያ እነዚህ ጣቶቼ እስከተንቀሳቀሱ ድረስ ክርስቲያኖችን በመዳፌ ሥር አስገብቼ ጨምድጄ እይዛቸዋለሁ" አለው። ይህንን ፉከራና ድንፋታ ያዳምጥ የነበረ አንድ ክርስቲያን እንዲህ ሲል መለሰለት፥ "አዎን ሁለቱን ጣቶችህን አይቻለሁ፤ በጣም የሚገርምህ ደግሞ አንተ የማታየውን ሌላ ነገር እኔ አያለሁ፤ ያም ጣት ብቻ ሳይሆን ትልቅ እጅ አያለሁ። ያም እጅ እኛን ሊጠብቅ የተዘረጋ የኃያሉ የእግዚአብሔር እጅ ነው። ያ ትልቅ እጅ እስካለ ድረስ ያንተ ትናንሽ ጣቶች እኛን አያስደነግጡንም።" መጽሀፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል" ይላል። ትግላችን መንፈሳዊ በመሆኑ ኃይላችን የሚመነጨው ከኃይሉ ከእግዚአብሔር ነው።

...................................................................